በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/ 218918

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡ 1ኛ/ አቶ ኃብተወልድ ተከተለው

2ኛ/ አቶ ደሳለኝ አበበ      የኒላወርቅ ተከተል -ቀረቡ

3ኛ/ አቶ እሱእንዳለው አየለ

ተጠሪ፡ ህዳሴ ቴሌኮም አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የአማራ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በዚህ ችሎት እንዲታረም በሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩ የደረጃ እድገት የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የደ/ብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበቡት ክስ ተጠሪ ሚያዝያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም ባወጣው የደረጃ እድገት እና የዝውውር ማስታወቂያ ለመወዳደር በተለያየ ስራ መደብ ላይ ተመዝግበን የነበርን ቢሆንም ተጠሪ ግን የአከባቢ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ የስራ መደብ ላይ ብቻ የደረጃ እድገት አወዳድሮ ተፈፃሚ ያደረገ ሲሆን

አመልካቾች ለመወዳደር ከተመዘገብንበት መደብ ላይ ያለ አግባብ ከደረጃ እድገት እና ዝውውር መታገዳችን ህገወጥ በመሆኑ በደረጃ እድገቱና ዝውውሩ ላይ ተሳታፊ እንዲንሆን ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች የገለጹት የደረጃ እድገትና ዝውውር ለሽያጭ አገልግሎት የሚሆን ምርቶችን የሚያቀርብለት ኢትዮ-ቴሌኮም የመዋቅር ለውጥ በማድረጉ ምክንያት የተጠሪ ድርጅት ከ3 ወደ 2 በመታጠፉ ማሻሻያዎችንም ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤በዚህ ምክንያት የደረጃ እድገትና ዝውውር እንዲቋረጥ የተወሰነ በመሆኑ የተፈፀመው ህገ ወጥ ተግባር የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር  እና ማስረጃ መርምሮ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ የደ/ብርሃን ከፍተኛ አከባቢ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለደቡብ ምስራቅ አዲስ አበባ ዲስትሪክት እንዲሆንና የደ/ብርሃን አካባቢ ጽ/ቤት ባለበት ይቀጥላል የሚል እንጂ የታጠፈ አወቃቀር አያሳይም፣ ለአመልካቾች በሰጠዉ ምላሽም ጉዳዩ ገና አልተቋጨም መክሰስ አትችሉም የሚለው ጋር የሚጋጭ ነው ፤የደረጃ እድገትና ዝውውር ማስታወቂያ የወጣም የአወቃቀር ማሻሻያው ከተደረገ ከመጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ.ም በኋላ ሚያዝያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም በመሆኑ ማስታወቂያው መመሪያውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ማስታወቂያው መሰረዙ ተገቢ ባለመሆኑ በማስታወቂያው መሰረት አመልካቾችም ተሳታፊ ሆነው የደረጃ እድገት እና ዝውውር ላይ አወዳድሮ ውጤቱን እንዲያሳውቋቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

ተጠሪ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ይታረምልኝ በማለት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ ችሎቱም ጉዳዩ የወል ወይስ የግል የስራ ክርክር ነው የሚለው ጭብጥ መርምሮ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2011 አንቀጽ 143(1)(ሰ) ላይ የወል የስራ ክርክር ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ዕድገትና ዝውውር አስመልክቶ አሰሪው የሚያወጣቸው አፈፃፀም ስርዓት ላይ የሚቀርቡ ክሶች የወል የስራ ክርክር መሆናቸውን እና በአዋጁ አንቀጽ 148(1)(ሀ) መሰረት የወል የስራ ክርክሮችን በሚመለከት አከራክሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ የቋሚ ቦርድ በመሆኑ የመደበኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በመሻር፣ አመልካቾች ስልጣን ላለው አካል ክስ ማቅረብ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡አመካልቾች የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡-የደረጃ እድገት እና ዝውውርን የሚመለከት ክርክር በአዋጁ አንቀጽ 139(1)(ሠ) መሰረት

የግል የስራ ክርክር መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 94889 ላይ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግን ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውንም አንቀጽ 143(1)(ሰ) የአፈፃፀም ስርዓቶች ጋር በማያያዝ ውሳኔ መስጠቱ ስህተት ነው፡፡እኛ ያቀረብነው ስለ ደረጃ እድገትና ዝውውር ውድድር እንጂ ከአፈፃፀም ስርዓት ጋር የተያያዘ ጥያቄ አላቀረብንም፤ ስለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ውሳኔ እንዲሻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ጥያቄዉ የደረጃ እድገት እና ዝውውር ማስታወቂያ መሰረት ተሳታፊ እንዳንሆን መታገዳችን አግባብ አይደለም የሚል የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት የወል ጥያቄ ስለሆነ ወሳኝ ቦርድ የሚቀርብ ነው በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከአዋጅ ቁ. 1156/2011 አንቀጽ 139(1)(ሠ) አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 30/05/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የደረጃ እድገትና ዝውውር አስመልክቶ አሰሪው በሚያወጣቸው የአፈፃፀም ስርዓቶች መመሪያዎች ላይ የሚቀርቡ ክሶች የወል የስራ ክርክር መሆናቸውን አንቀጽ 143(1)(ሰ) ያመላክታል፤የአመልካቾች ቅሬታም ተጠሪ ባወጣው የደረጃ እድገትና ዝውውር ተሳታፊ እንዲሆን የሚል በመሆኑ ይህም የአፈፃፀም ስርዓቶች መመሪያዎች ላይ የቀረበ ክስ መሆኑ ነው እንጂ ያገኘነው እድገት ተከለከልን የሚል ስላልሆነ ይህ የክርክር ውጤቱ የሌሎች ሰራተኞችንም በማስታወቂያው መሰረት አብረው ለእድገቱ የሚወዳደሩትን ጭምር መብት የሚነካ ውጤቱ በተከራካሪዎች ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ባለመሆኑ በዚህ አንቀጽ ስር የሚወድቅ የወል የሥራ ክርክር ነው፡፡ስለዚህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ትክክልና የማይነቀፍ ስለሆነ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ አመልካቾች ክስ ፍሬነገር የሚያሳዉ ተጠሪ ባወጣዉ የደረጃ እድገት ለመወዳደር ከተመዘገብን በኋላ መታገዳችን ተገቢ ባለመሆኑ በዉድድሩ እንዲንሳተፍ ይወሰን የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መከራከሪያ ለዉድድር ማስታወቂያ ማዉጣቱን አምኖ ነገር ግን ዉድድሩ ለጊዜዉ ተፈጻሚ እንዳይሆን የተደረገዉ ለሽያጭ የሚሆን ምርቶችና አገልግሎቶችን ከሚያቀርብለት ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተጣጣመ አደረጃጀት እንዲኖር እና ድርጅቱን ከኪሳራ ለመታደግ ታስቦ ነዉ በማለት ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬነገሩ ላይ አከራክርዉ የሰጡትን ዉሳኔ የመረመረዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ከግራ ቀኙ ክርክር ይዘት በመነሳት ዉድድሩ የተሰረዘዉ ከመዋቅር ለዉጥ ጋር በተያያዘ በመሆኑ የደረጃ እድገትና ዝዉዉር የአፈጻጸም ስርዓት የሚመለከት ጉዳይ የወል የስራ ክርክር እንጂ የግል የስራ ክርክር አይደለም በሚል የስራ ክርክር ችሎት የዳኝነት ስልጣን የለዉም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡በዚህ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የዳኝነት ስልጣን የሚወሰነዉ በቀረበዉ ክስ ወይም የክስ ምክንያት ነዉ፡፡ነገር ግን ተከሳሹ ባቀረበዉ ክርክር ወይም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ምክንያት የዳኝነት ስልጣን ሊለዉጥ እንደሚችል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ክሱ ለስራ ክርክር ችሎት የቀረበዉ ከዉድድር ታግደናል በማለት ስለሆነ የግል የስራ ክርክር ነዉ በሚል መነሻ የቀረበ መሆኑን ያሣያል፡፡የግል የስራ ክርክር በመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ስለመሆኑ እንዲሁም የወል ሥራ ክርክር ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታይ መሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ላይ ተመልክቷል፡፡(አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 138 ና 139 እና 147(1) ይመለከታል)፡፡ይሁንና ምላሽ የሚሻው ጥያቄ አንድ ጉዳይ የግል ወይም የወል የሥራ ክርክር ሊባል የሚችልበት አግባብ ምንድነዉ? የሚለዉ ነው፡፡በዚህ ረገድ አዋጁ ቀጥተኛ ትርጉም የሚሰጥ ሳይሆን በጉዳዮቹ አይነት በመዘርዘር ያመላከተ ስለሆነ አንዳንድ ጉዳዮችን የወል ወይም የግል በሚል ለመለየት ቀላል አይደለም፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት ስለ ግል የሥራ ክርክርና ስለ ወል የሥራ ክርክር መለየት የሚቻልበትን ሁኔታ እና  የክልልም ሆነ የፌዴራል የሥራ ክርክር ችሎቶች የግል የሥራ ክርክሮችን በዳኝነት አይተው የመወሰን ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በሚመለከት  መዝገብ ቁጥር 18180 ቅጽ1 የሰጠው አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ እና በሌሎች መዝገቦች የተሰጠዉ ዉሳኔ ወል ወይም የግል ስራ ክርክር ለመለየት ረገድ በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይም ተፈጻሚ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ሰበር መ/ቁ/ 78865 ቅጽ 14 እና ሌሎች መሰል መዝገቦችን መመልከት ይቻላል፡፡በእርግጥ ሰበር ችሎቱ ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ አዋጅ ቁጥር 377/96  አሁን በአዋጅ ቁጥር 1156/2013 የተተካ ቢሆንም የወል ወይም የግል የስራ ክርክር ምንነት እና ዳኝነት ስልጣን ላይ በሁለቱ አዋጆች መካከል መሰረታዊ የይዘት ለዉጥ ባለመኖሩ የሰበር ችሎቱን የህግ ትርጉም ተፈጻሚነት አላስቀረም፡፡ስለዚህም ክርክሩን የወል ወይም የግል የስራ ክርክር ነዉ የሚያሰኘዉ የተከራካሪዎቹ (ሰራተኛ) ቁጥር ማነስ ወይም መብዛት ሳይሆን የተጠየቀዉ ዳኝነት ወይም የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዉጤቱ ከተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ሰራተኞች

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መብትና እና ጥቅም ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ዉጤት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑ ላይ የሚወሰን ነዉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ የአመልካቾች ክስ ምክንያት ከዉድድር ያለአግባብ ታግደናል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩ ከድርጅቱ መዋቅር ጋር በተያያዘ ዉድድሩ እንዳይፈጸም መታገዱን ገልጾ መከራከሩን ተከትሎ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የደረጃ እድገትና እና ዝዉዉር ማስታወቂያ በተጠሪ አስተዳደራዊ ዉሳኔ መሰረዙን አረጋግጧል፡፡ማስታወቂያዉ የተሰረዘዉ ከድርጅቱ መዋቅር ወይም ሌላ የፖሊሲ ዉሳኔ ጋር በተያያዘ ነዉ ከተባለ የአመልካቾች የግል ጉዳይ አይደለም ማለት ነዉ፡፡የዉድድር ማስታወቂያ በዚህ መነሻ መሰረዙ ከተረጋገጠ ደግሞ ዉጤቱ አመልካቾችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተወዳዳሪዎችንም የሚመለከት ነዉ፡፡ስለዚህም ክርክሩ አመልካቾች ከዉድድር መታገድ አለመታገድ ጉዳይ ሳይሆን የዉድድር ማስታወቂያዉን መሰረዝ ተገቢ መሆን አለመሆኑን የመመርመር ጉዳይ ይሆናል፡፡እንዲህ ሲሆን ደግሞ ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር ባህርይ ይኖረዋል ማለት ነዉ፡፡በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠዉ ፍሬነገር ምክንያት ጉዳዩ የግል መሆኑ ቀርቶ የወል የስራ ክርክር ከሆነ ደግሞ መደበኛዉ ፍርድ ቤት ስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን የማየት የስረነገር ዳኝነት ስልጣን የለዉም፡፡ሰበር አጣሪ ችሎትም ሆነ አመልካቾች የጠቀሱት የሰበር መ/ቁ/ 94889 ላይ ጉዳዩ የግል የስራ ክርክር ነዉ ተብሎ ዉሳኔ የተሰጠዉ የደረጃ እድገት ዉድድሩን ያሸነፈችዉ ሰራተኛ  ምደባና ክፍያ ተከልክያለሁ በማለት ያቀረበችዉን ዳኝነት የሚመለከት በመሆኑ ነዉ፡፡ይህ ጉዳይ አሁን ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር በፍሬነገር ደረጃ ተመሳሳይ ባለመሆኑ ተጠቃሹ መዝገብ ዉሳኔ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ከዉድድር ያለአግባብ ታገድናል የሚል ቢሆንም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠዉ ፍሬነገር ዉድድሩ እንዲሰረዝ ተደረገዉ ከተጠሪ ድርጅት መዋቅር ጋር በተያያዘ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩ የወል ስራ ክርክር ነዉ በሚል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጁ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 (1/ሐ/ እና ወይም መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1ኛ/የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር በመ/ቁጥር108753 ላይ በቀን04/02/2014ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም